# የ7ኛ ክፍል ክትባቶችን በሚመለከት አስፈላጊ መረጃ

ውድ ወላጅ/አሳዳጊ

የህብረተሰብ ጤና በትምህርት ቤቶች ለሚገኙ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በመኸርና በፀደይ ወራት ነፃ ክትባት ይሰጣል፡፡

የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚከተሉትን በሽታዎች ለመከላከል የሚረዷቸው ሦስት አስፈላጊ ክትባቶች ይሰጧቸዋል፡

- **የሜኒንጎኮካል በሽታ** (ማጅራት ገትር ያስከትላል)*ትምህርት ለመከታተል ያስፈልጋል*
- **ሄፐታይተስ ቢ** (የጉበት ጉዳት እና ጉበት ካንሰር ያመጣል)
- **ሂዩማን ፓፒሎማቫይረስ** (HPV፤ ቅድመ ካንሰር ቁስሎችን፣ የአፍ፣ የመራቢያ አካላት እና የፊንጢጣ ካንሰር እና የመራቢያ አካላት ላይ የሚወጣ ኪንታሮትን ያስከትላል)

ልጅዎን የእዚህን በሽታዎች መከላከያ ክትባት እንዲያስከትቡ አጥብቄ እመክራለሁ፡፡ ክትባቶቹ ደህንነታቸው የተጠበቀና ውጤታማ ሲሆኑ ተከታታይ ክትባቶቹን በተሟላ ሁኔታ መውሰድ ለህይወት አስጊ በሆኑ በሽታዎች የመያዝ አደጋንም በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል፡፡

ከዚህ በታች ያሉትን እንዲያደርጉ እጠይቃለሁ፡

- wdgpublichealth.ca/immunizeGr7 ላይ የሚገኘውን የክትባቱን መረጃ እንዲያነቡ
- በተቻለ ፍጥነት ለልጅዎ የኦንላየን የስምምነት ቅፅ ይሙሉ *wdgpublichealth.ca/gr7consent*

ልጅዎ ከላይ ከተዘረዘሩት ክትባቶች ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን ከወሰደ፣ እባክዎ የስምምነት ቅፁን ይሙሉ እና በቅፁ ላይ ክትባቱን የወሰደባቸውን ቀናት ያመልክቱ፡፡ የህብረተሰብ ጤና ነርስ ለልጅዎ ክትባቱን የምትሰጠው ክትባቱ አሁንም የሚያስፈልግ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

የህብረተሰብ ጤና ትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጡ ክትባቶች ለተማሪዎች አዎንታዊ ልምድ እንዲሆኑ ይፈልጋል፡፡ ይህንን ፕሮግራም በሚመለከት ጥያቄ ካለዎት ወይም የስምምነት ቅፁን ለመሙላት ድጋፍ የሚያስፈልግዎ ከሆነ፣ እባክዎ የህብረተሰብ ጤና ነርስን ለማናገር ወደ ዌሊንግተን-ዱፍሪን-የህብረተሰብ ጤና በ 1-800-265-7293 ኤክስቴንሽን 7006 ይደውሉ፡፡

ከሰላምታ ጋር

**ዶ/ር ማቲው ቴንንባዉም,** MD, CCFP, MPH, FRCPC

**ተባባሪ የጤና ሜዲካል ኦፊሰር**

160 Chancellors Way, Guelph, ON N1G 0E1

**T:** 1-800-265-7293 | **F:** 519-836-7215 | **wdgpublichealth.ca**

# የሄፐታይተስ ቢ ክትባት

**ከሄፐታይተስ ቢ ቫይረስ ይከላከላል፡፡**

## ሄፐታይተስ ቢ ምንድን ነው?

ሄፐታይተስ ቢ ከባድ የጉበት በሽታዎችን የሚያስከትል ቫይረስ ሲሆን ቋሚ የሆነ የጉበት ጉዳት፣ ኪሮሲስ እና/ወይም የጉበት ካንሰር ሊያስከትል ይችላል፡፡ ሄፐታይተስ ቢ ካናዳ ውስጥ ዋነኛው የጉበት ካንሰር መንስዔ ነው፡፡

ሄፐታይተስ ቢ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፈው በበሽታው ከተያዘ ሰው ደም እና የሰውነት ፈሳሾች ጋር በሚደረግ ንክኪ ነው፡፡ በግብረ ሥጋ ግንኙነት፣ መርፌን በጋራ በመጠቀም፣ የተበከሉ መሳሪያዎችን ለንቅሳት እና ለመብሳት በመጠቀም እና የጥርስ ብሩሽን ወይም ምላጭን በጋራ በመጠቀም ሊተላለፍ ይችላል፡፡ በተጨማሪም በወሊድ ወቅት ከእናት ወደልጅ ሊተላለፍ ይችላል፡፡

## መከተብ ለምን?

ክትባት እርስዎንና ቤተሰብዎን ከከባድ በሽታዎች የመከላከያ ምርጥ መንገድ ነው፡፡ ይህ ክትባት ለበሽታው ከመጋለጥ በፊት ቢወሰድ የበለጠ ውጤታማ ይሆናል፡፡

ሄፐታይተስ ቢ መድሀኒት የለውም፡፡ በተጨማሪም በበሽታው ከተያዙ 10 ሰዎች ውስጥ አንዱ እድሜ ልኩን ከበሽታው ጋር ይኖራል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ግለሰቦች ምልክቶችን የማያሳዩ ሲሆን በሽታውን ለሌሎች ያስተላልፋሉ፡፡

ክትባቱ በሚመከረው ዶዝ ሲሰጥ 98 በመቶ የሚሆኑ ሰዎችን ከበሽታው ይከላከላል፡፡

## ለመከተብ ብቁ የሆነው ማን ነው?

ክትባቱ በመደበኛነት ለ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሰጥ ሲሆን ክትቱን ለመውሰድ ያላቸው ብቁነት 12ኛ ክፍልን እስኪጨርሱ ድረስ ይቀጥላል፡፡ ይህ ክትባት ዕድሜያቸው ከ11 እስከ 15 ዓመት ለሚሆን ተማሪዎች በሁለት-ዶዝ በተከታታይ በ4-6 ወራት ልዩነት ይሰጣል፡፡ ተከታታይ ክትባታቸውን የጀመሩ ወይም ያጠናቀቁ ዕድሜያቸው 16 እና ከዚያ በላይ የሆነ ተማሪዎች ሦስት ዶዝ ክትባት ያስፈልጋቸዋል፡፡

የሄፐታይተስ ቢ ክትባት በከፍተኛ ሁኔታ ተጋላጭ ለሆኑ ጨቅላ ህፃናት፣ ልጆች እና አዋቂዎች በነፃ ይሰጣል፡፡ ብቁነትን በሚመለከት የበለጠ መረጃ ለማግኘት ለኦንታሪዮ በመንግሥት የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጥ ክትባት መርሀ ግብር ን ሰንጠረዥ 3 ይመልከቱ፡፡

ክትባቱ የሙያ አደጋዎች ላሉባቸው፣ ሄፐታይተስ ቢ በከፍተኛ ደረጃ በሚገኝባቸው ሀገራት ለሚኖሩ፣ ለሚጓዙ ወይም የህክምና ሂደት/እንክብካቤ ለሚያደርጉ፣ እና በሄፐታይተስ ቢ የመያዝ አደጋን መቀነስ ለሚፈልጉ ሰዎች ይመከራል ነገር ግን በነፃ አይሰጥም፡፡

ማስታወሻ: ተከታታይ ክትባቶች ከተወሰዱ መደበኛ ማበረታቻዎችን መውሰድ አይመከርም፡፡

## ክትባቱን መውሰድ የሌለባቸው እነማን ናቸው?

- የክትባቱ ማንኛውም ክፍል ወይም መያዣው ከባድ አለርጂ የሚያስከትልበት ማንኛውም ሰው፡፡
- ከዚህ በፊት በዚህ ክትባት ምክንያት ከባድ አለርጂ የተከሰተበት ሰው፡፡
- ከፍተኛ ትኩሳት ወይም ከጉንፋን የከፋ በሽታ የያዘው ማንኛውም ሰው፡፡
- ሄፐታይተስ ቢን የያዘ የሄፐታይተስ ቢ ወይም ጥምር ተከታታይ ክትባት ያጠናቀቀ ማንኛውም ሰው (Twinrix®, Infanrix Hexa®).

እርጉዝ ከሆኑ፣ የሚያጠቡ ከሆነ ወይም ከዚህ ቀደም ክትባት በወሰዱ በሁለት ሳምንታት ውስጥ በጉሊያን-ባሬ ሲንድረም (GBS) ተይዘው የሚያውቁ ከሆነ እባክዎ ይህንን ክትባት ስለመከተብ ለጤና እንክብካቤ ሰጪ ያማክሩ፡፡

PublicHealth
WELLINGTON-DUFFERIN-GUELPH
Stay Well.

1-800-265-7293
info@wdgpublichealth.ca
wdgpublichealth.ca

## ከክትባት በኋላ ምን ይጠበቃል?

የሄፐታይተስ ቢ ክትባት ደህንነቱ የተጠበቀና ሊቋቋሙት የሚችሉት ነው፡፡ የጎንዮሽ ጉዳቶች የሚከሰቱ ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ ቀላል እና በጥቂት ቀናት ውስጥ የሚተዉ ናቸው፡፡

የተለመዱ የጎንዮሽ ጉዳቶች መርፌ የተወጋበት ቦታ መቅላት፣ ማበጥ እና/ወይም ህመምን ያካትታሉ፡፡

ራስ ምታት፣ ትኩሳት፣ ድካም፣ መደንዘዝ፣ ማቅለሽለሽ እና የጡንቻ ህመም ሊከሰቱ የሚችሉ ቢሆንም ብዙም የተለመዱ አይደሉም፡፡

ምንም እንኳን ያልተለመዱ ቢሆንም ከባድ አለርጂዎች (ማለትም አናፍላክሲስ) ማንኛውም ክትባት ሲወሰድ ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ አናፍላክሲስ የሚከሰትበት በጣም የተለመደው ጊዜ ክትባት ከወሰዱ በኋላ ባሉት 15 ደቂቃዎች በመሆኑ በዚህ ጊዜ ውስጥ በክሊኒክ አካባቢ መቆየት ይመከራል፡፡

## ክትባትዎን በሚመለከት መረጃ ይኑርዎት

ክትባት ከተከተቡ በኋላ የጤና እንክብካቤ ሰጪዎ የግል ክትባት መዝገብዎ (ቢጫ ካርድ) ላይ ይህን መረጃ ማስቀመጡን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡ ካርዱን ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ያስቀምጡ፡፡ልጅዎ ፍቃድ ያለው የልጆች ማቆያ ወይም ትምህርት ቤት የሚውል ከሆነ ክትባት በሚሰጥበት ጊዜ እባክዎ ለህብረተሰብ ጤና ያሳውቁ፡፡ ስለክትባቶቹ ከሚከተሉት በአንዱ መንገድ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ፡

- **ኦንላየን:** immunizewdg.ca ላይ የሚገኘው ኢሚውናይዜሽን ኮኔክት ኦንታሪዮ (ICON) መሳሪያ ሪፖርት ለማድረግ እና የልጅዎን የክትባት መዝገብ ለማየት ያስችልዎታል፡፡
- **ኢሜይል:**vaccine.records@wdgpublichealth.ca
- **ስልክ:** 1-800-265-7293 ኤክስቴንሽን 4396
- **ፋክስ:** 1-519-836-2986

## ለበለጠ መረጃ የሚከተሉትን ይጎብኙ:

- ዊሊንግተን-ዱፍሪን-ጉልፍ ህብረተሰብ ጤና: wdgpublichealth.ca
- የኦንታሪዮ የጤና ሚኒስቴር: www.ontario.ca/page/vaccines
- ኢሚዩናይዝ ካናዳ: www.immunize.ca
- ለኦንታሪዮ በመንግሥት የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጥ የክትባት መርሀ ግብር:

# የሂዩማን ፓፒሎማ ቫይረስ ክትባት (HPV-9)

**ከ 9 HPV ዓይነቶች ማለት ከ HPV - 6, 11, 16, 18, 31, 33, 45, 52, እና 58 ይከላከላል፡፡**

## HPV ምንድን ነው?

HPV የማህፀን በር፣ የሴት ብልት የውጪኛው ክፍል፣ የሴት ብልት፣ ፊንጢጣ፣ ጭንቅላት፣ አንገት፣ የወንድ ብልት ካንሰርን የሚያመጣ የተለመደ ቫይረስ ሲሆን የመራቢያ አካላት ላይ የሚወጣ ኪንታሮትንም ሊያስከትል ይችላል፡፡ በጾታዊ ግንኙነት ጊዜ የሚተላለፍ ሲሆን በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም በጾታዊ ንክኪ ይተላለፋል፡፡ ብዙ ሰዎች ሳይከተቡ ከ HPV ጋር እድሜ ልካቸውን ይኖራሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ HPV በሽታ በራሱ ጊዜ ይጠፋል፡፡ አንዳንድ ሰዎች HPV የማይለቃቸው ሲሆን ከ HPV ጋር ለተገናኙ ካንሰሮች ወይም የመራቢያ አካላት ላይ ለሚወጣ ኪንታሮት ያጋልጣቸዋል፡፡ አብዛኛውን በ HPV የተያዙ ሰዎች ምንም ዓይነት ምልክቶችን የማያሳዩ ሲሆን ቫይረሱን ሳያውቁ ለሌሎች ሊያስተላልፉ ይችላሉ፡፡

## መከተብ ለምን?

ክትባት እርስዎንና ቤተሰብዎን ከከባድ በሽታዎች የመከላከያ ምርጥ መንገድ ነው፡፡ ይህ ክትባት ለበሽታው ከመጋለጥ በፊት ቢወሰድ የበለጠ ውጤታማ ይሆናል፡፡

HPV-9 ተከታታይ ክትባቶችን በማጠናቀቅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ከ HPV ጋር ተያያዥነት ያላቸውን በጣም የተለመዱ በሽታዎችን መከላከል እንደሚቻል ተረጋግጧል፡

- ከ 90 በመቶ በላይ የሚሆነውን የማህፀን በር ካንሰር
- ከ 80-90 በመቶ የሚሆነውን የፊንጢጣ ካንሰር
- 40 በመቶ የሚሆነውን የሴት ብልት እና የሴት ብልት የውጪኛው ክፍል ካንሰር
- ከ 40-50 በመቶ የሚሆነውን የወንድ ብልት ካንሰር
- ከ 25-35 በመቶ የሚሆነውን የአፍ እና የጉሮሮ ካንሰሮች (ከአፍና ጉሮሮ ጋር የተያያዙ ካንሰሮች)
- ከ 90 በመቶ በላይ የሚሆነውን የመራቢያ አካላት ላይ የሚወጣ ኪንታሮት

ምንም እንኳ የHPV ክትባት ቢወስዱም የማህፀን በር፣ የሴት ብልት የውጪኛው ክፍል፣ የሴት ብልት፣ የፊንጢጣ፣ የወንድ ብልት እና አንዳንድ የጭንቅላትና አንገት ካንሰሮች ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ሴቶች መደበኛ የማህፀን በር ካንሰር ምርመራ ማድረግ አለባቸው፡፡

## ለመከተብ ብቁ የሆነው ማን ነው?

ክትባቱ በመደበኛነት ለ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሰጥ ሲሆን ክትባቱን ለመውሰድ ያላቸው ብቁነት 12ኛ ክፍልን እስኪጨርሱ ድረስ ይቀጥላል፡፡

በተጨማሪም ክትባቱ ዕድሜያቸው ከ 9-45 ለሚሆን ሴቶች እና ዕድሜያቸው 9-26 ለሚሆን ወንዶች እንዲሁም ዕድሜያቸው 27 እና ከዚያ በላይ ለሚሆን ተጋላጭነታቸው ቀጣይ ለሆነ ሰዎች ይመከራል፡፡

ይህ ክትባት የሚሰጠው ዕድሜያቸው ከ 9-14 ዓመት ለሚሆኑ ታዳጊዎች በስድስት ወር ልዩነት ተከታታይ ሁለት-ዶዝ እና ዕድሜያቸው 15 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆናቸው ደግሞ በ6 ወራት ውስጥ (0፣2፣6) ተከታታይ ሦስት-ዶዝ ይሰጣል፡፡

ዕድሜያቸው ከ 9-14 ዓመት የሚሆን ታዳጊዎችን ጨምሮ በሽታ የመከላከል አቅማቸው የደከመ ሰዎች ሦስት-ዶዝ መውሰድ አለባቸው፡፡

## ክትባቱን መውሰድ የሌለባቸው እነማን ናቸው?

- የክትባቱ ማንኛውም ክፍል ወይም መያዣው ከባድ አለርጂ የሚያስከትልበት ማንኛውም ሰው፡፡
- ከዚህ በፊት በዚህ ክትባት ምክንያት ከባድ አለርጂ የተከሰተበት ሰው፡፡
- ከፍተኛ ትኩሳት ወይም ከጉንፋን የከፋ በሽታ የያዘው ማንኛውም ሰው፡፡

እርጉዝ ከሆኑ፣ የሚያጠቡ ከሆነ ወይም ከዚህ ቀደም ክትባት በወሰዱ በሁለት ሳምንታት ውስጥ በጉሊያን-ባሬ ሲንድረም (GBS) ተይዘው የሚያውቁ ከሆነ እባክዎ ይህንን ክትባት ስለመከተብ ለጤና እንክብካቤ ሰጪ ያማክሩ፡፡

PublicHealth
WELLINGTON-DUFFERIN-GUELPH
Stay Well.

1-800-265-7293
info@wdgpublichealth.ca
wdgpublichealth.ca

## ከክትባት በኋላ ምን ይጠበቃል?

የኤችፒቪ-9 ክትባት ደህንነቱ የተጠበቀና ሊቋቋሙት የሚችሉት ነው፡፡

የጎንዮሽ ጉዳቶች የሚከሰቱ ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ ቀላል እና በጥቂት ቀናት ውስጥ የሚተዉ ናቸው፡፡ የተለመዱ የጎንዮሽ ጉዳቶች መርፌ የተወጋበት ቦታ መቅላት፣ ማበጥ እና/ወይም ህመምን ያካትታሉ፡፡

ራስ ምታት፣ ትኩሳት፣ ድካም፣ መደንዘዝ፣ ማቅለሽለሽ እና የጡንቻ ህመም ሊከሰቱ የሚችሉ ቢሆንም ብዙም የተለመዱ አይደሉም፡፡

ምንም እንኳን ያልተለመዱ ቢሆንም ከባድ አለርጂዎች (ማለትም አናፍላክሲስ) ማንኛውም ክትባት ሲወሰድ ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ አናፍላክሲስ የሚከሰትበት በጣም የተለመደው ጊዜ ክትባት ከወሰዱ በኋላ ባሉት 15 ደቂቃዎች በመሆኑ በዚህ ጊዜ ውስጥ በክሊኒክ አካባቢ መቆየት ይመከራል፡፡

## ክትባትዎን በሚመለከት መረጃ ይኑርዎት

ክትባት ከተከተቡ በኋላ የጤና እንክብካቤ ሰጪዎ የግል ክትባት መዝገብዎ (ቢጫ ካርድ) ላይ ይህን መረጃ ማስቀመጡን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡ ካርዱን ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ያስቀምጡ፡፡

ልጅዎ ፍቃድ ያለው የልጆች ማቆያ ወይም ትምህርት ቤት የሚውል ከሆነ ክትባት በሚሰጥበት ጊዜ እባክዎ ለህብረተሰብ ጤና ያሳውቁ፡፡ ስለክትባቶቹ ከሚከተሉት በአንዱ መንገድ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ:

- **ኦንላየን:** immunizewdg.ca ላይ የሚገኘው የኦንታሪዮ ኢሚውናይዜሽን ኮኔክት (ICON) መሳሪያ ሪፖርት ለማድረግ እና የልጅዎን የክትባት መዝገብ ለማየት ያስችልዎታል፡፡
- **ኢሜይል:**vaccine.records@wdgpublichealth.ca
- **ስልክ:**1-800-265-7293 ኤክስቴንሽን 4396
- **ፋክስ:** 1-519-836-2986

## ለበለጠ መረጃ የሚከተሉትን ይጎብኙ:

- ዌሊንግተን-ዱፍሪን-ጉልፍ ህብረተሰብ ጤና: wdgpublichealth.ca
- የኦንታሪዮ የጤና ሚኒስቴር: www.ontario.ca/page/vaccines
- ኢሚዩናይዝ ካናዳ: www.immunize.ca
- ለኦንታሪዮ በመንግሥት የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጥ የክትባት መርሀ ግብር: www.health.gov.on.ca/en/pro/programs/immunization/schedule.aspx

# የሜኒንጎኮካል ክትባት
# (Men-C-ACYW-135)

**በሴሮ ግሩፕስ A, C, Y, እና W-135 ምክንያት ከሚከሰት ተስፋፊ የሜኒንጎኮካል በሽታ ይከላከላል፡፡**

## የሜኒንጎኮካል በሽታ ምንድን ነው?

የሜኒንጎኮካል በሽታ ኔሴሪያ ሜኒንጃይቲዲስ በሚባል ባክቴሪያ አማካኝነት የሚመጣ በሽታ ነው፡፡ ከባድ ህመም የሚያስከትሉ አምስት የተለመዱ ዝርያዎች አሉ፡ A, B, C, Y እና W-135፡፡ እነዚህ ባክቴሪያዎች የአንጎል እና የህብለ ሰረሰርን ሽፋን የሚያጠቃ ማጅራ ገትር የሚባል በሽታ እና/ወይም ሴፕሲስ ተብሎ የሚጠራ አብዛኛውን ጊዜ የአካል ጉዳትን የሚያስከትል የደም በሽታ ሊያመጡ ይችላሉ፡፡

ባክቴሪያዎቹ በመሳል ወይም በማስነጠስ ወቅት ከሰውነት ወደ አየር በሚወጡ ጠብታዎች ወይም በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር በሚደረግ ቀጥተኛ ግንኙነት ምክንያት ይተላለፋሉ፡፡ ይህ መሳሳም ወይም ምግብ፣ ማንኪያ፣ ቢላ፣ ሹካ የመሳሰሉ መመገቢያ ቁሳቁሶችን፣ መጠጦችን፣ ኤሌክትሮኒክ ሲጋራን የመሳሰሉ ዕቃዎችን መጋራትን ያካትታል፡፡

በግምት 10 በመቶ የሚሆኑ ጤናማ ሰዎች ህመም ሳይሰማቸው ባክቴሪያውን በአፍንጫቸው ወይም በጉሮሯቸው ይዘው ይኖራሉ ነገር ግን ባክቴሪያውን ወደሌሎች ሊያስተላልፉ ይችላሉ፡፡

በሜኒንጎኮካል ምክንያት የሚከሰቱ ውስብስብ የጤና ችግሮች ቋሚ የሆነ የመስማት ችግር፣ የአዕምሮ እክሎች እና እጅ እና እግር መቆረጥን ሊያካትቱ ይችላል፡፡ የሜኒንጎኮካል በሽታ በበሽታው ከተያዙ 100 ሰዎች ውስጥ አንዱን ይገድላል፡፡

## መከተብ ለምን?

ክትባት እርስዎንና ቤተሰብዎን ከከባድ በሽታዎች የመከላከያ ምርጥ መንገድ ነው፡፡ ይህ ክትባት ለበሽታው ከመጋለጥ በፊት ቢወሰድ የበለጠ ውጤታማ ይሆናል፡፡

ክትባቱ ከአራቱ የተለመዱ እና አስከፊ የሜኒንጎኮካል በሽታ ዝርያዎች ይከላከላል- A, C, Y, እና W-135፡፡ ውጤታማነቱም ከ 80-85 በመቶ ነው፡፡

ልጅዎ በህፃንነቱ የሜኒንጎኮካል ኮንጁጌት ሲ (Men-C-C) ክትባት የወሰደ ከሆነ፣ ከተጨማሪ ዝርያዎች የሚከላከል ስለሆነ የMen-C-ACYW-135 ክትባትን መውሰድ አለበት፡፡

## ለመከተብ ብቁ የሆነው ማን ነው?

ክትባቱ በመደበኛነት ለ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሰጥ ሲሆን ክትባቱን ለመውሰድ ያላቸው ብቁነት 12ኛ ክፍልን እስኪጨርሱ ድረስ ይቀጥላል፡፡ ይህ ክትባት የሚሰጠው በነጠላ ዶዝ ነው፡፡

በተጨማሪም ክትባቱ አንዳንድ የህክምና ሁኔታዎች ላሉባቸው ወይም በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበራቸውን ለመሳሰሉ በከፍተኛ ሁኔታ ለሜኒንጎኮካል በሽታ ተጋላጭ ለሆኑ ልጆች እና አዋቂዎች በነፃ ይሰጣል፡፡ ብቁነትን በሚመለከት የበለጠ መረጃ ለማግኘት ለኦንታሪዮ በመንግሥት የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጥ ክትባት መርሀ ግብር ን ሰንጠረዥ 3 ይመልከቱ፡፡

ክትባቱ የሙያ አደጋዎች ላሉባቸው፣ የሜኒንጎኮካል በሽታ በከፍተኛ ደረጃ በሚገኝባቸው ሀገራት ለሚኖሩ ወይም ለሚጓዙ እና በሜኒንጎኮካል A, C, Y እና W-135 ዝርያዎች የመያዛቸውን አደጋ መቀነስ ለሚፈልጉ ሰዎች ይመከራል ነገር ግን በነፃ አይሰጥም፡፡

በጊዜ ሂደት የክትባቱ ውጤታማነት እንደሚቀንስ መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ ተጋላጭነታቸው ቀጣይ ለሆነ ሰዎች በየ 5 ዓመቱ የማበረታቻ ዶዞችን መውሰድ ይመከራል፡፡

## ክትባቱን መውሰድ የሌለባቸው እነማን ናቸው?

- የክትባቱ ማንኛውም ክፍል ወይም መያዣው ከባድ አለርጂ የሚያስከትልበት ማንኛውም ሰው፡፡
- ከዚህ በፊት በዚህ ክትባት ምክንያት ከባድ አለርጂ የተከሰተበት ሰው፡፡
- ከፍተኛ ትኩሳት ወይም ከጉንፋን የከፋ በሽታ የያዘው ማንኛውም ሰው፡፡
- ባለፉት አራት ሳምንታት ውስጥ ሌላ Men-C-C ክትባት የወሰደ ማንኛውም ሰው፡፡

እርጉዝ ከሆኑ፣ የሚያጠቡ ከሆነ ወይም ከዚህ ቀደም ክትባት በወሰዱ በሁለት ሳምንታት ውስጥ በጉሊያን-ባሬ ሲንድረም (GBS) ተይዘው የሚያውቁ ከሆነ እባክዎ ይህንን ክትባት ስለመከተብ ለጤና እንክብካቤ ሰጪ ያማክሩ፡፡

PublicHealth
WELLINGTON-DUFFERIN-GUELPH
Stay Well.

1-800-265-7293
info@wdgpublichealth.ca
wdgpublichealth.ca

## ከክትባት በኋላ ምን ይጠበቃል?

Men-C-ACYW-135 ክትባት ደህንነቱ የተጠበቀና ሊቋቋሙት የሚችሉት ነው፡፡

የጎንዮሽ ጉዳቶች የሚከሰቱ ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ ቀላል እና በጥቂት ቀናት ውስጥ የሚተዉ ናቸው፡፡የተለመዱ የጎንዮሽ ጉዳቶች መርፌ የተወጋበት ቦታ መቅላት፣ ማበጥ እና/ወይም ህመምን ያካትታሉ፡፡

ራስ ምታት፣ ትኩሳት፣ ድካም፣ መደንዘዝ፣ ማቅለሽለሽ እና የጡንቻ ህመም ሊከሰቱ የሚችሉ ቢሆንም ብዙም የተለመዱ አይደሉም፡፡

ምንም እንኳን ያልተለመዱ ቢሆንም ከባድ አለርጂዎች (ማለትም አናፍላክሲስ) ማንኛውም ክትባት ሲወሰድ ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ አናፍላክሲስ የሚከሰትበት በጣም የተለመደው ጊዜ ክትባት ከወሰዱ በኋላ ባሉት 15 ደቂቃዎች በመሆኑ በዚህ ጊዜ ውስጥ በክሊኒክ አካባቢ መቆየት ይመከራል፡፡

## ክትባትዎን በሚመለከት መረጃ ይኑርዎት

ክትባት ከተከተቡ በኋላ የጤና እንክብካቤ ሰጪዎ የግል ክትባት መዝገብዎ (ቢጫ ካርድ) ላይ ይህን መረጃ ማስቀመጡን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡ ካርዱን ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ያስቀምጡ፡፡

ልጅዎ ፍቃድ ያለው የልጆች ማቆያ ወይም ትምህርት ቤት የሚውል ከሆነ ክትባት በሚሰጥበት ጊዜ እባክዎ ለህብረተሰብ ጤና ያሳውቁ፡፡ ስለክትባቶቹ ከሚከተሉት በአንዱ መንገድ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ፡

- **ኦንላየን:** immunizewdg.ca ላይ የሚገኘው የኦንታሪዮ ኢሚውናይዜሽን ኮኔክት (ICON) መሳሪያ ሪፖርት ለማድረግ እና የልጅዎን የክትባት መዝገብ ለማየት ያስችልዎታል፡፡
- **ኢሜይል:**vaccine.records@wdgpublichealth.ca
- **ስልክ:**1-800-265-7293 ኤክስቴንሽን 4396
- **ፋክስ:** 1-519-836-2986

## ለበለጠ መረጃ የሚከተሉትን ይጎብኙ:

- ዌሊንግተን-ዱፍሪን-ጉልፍ ህብረተሰብ ጤና: wdgpublichealth.ca
- የኦንታሪዮ የጤና ሚኒስቴር: www.ontario.ca/page/vaccines
- ኢሚዩናይዝ ካናዳ: www.immunize.ca
- ለኦንታሪዮ በመንግሥት የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጥ የክትባት መርሀ ግብር: www.health.gov.on.ca/en/pro/programs/immunization/schedule.aspx

PublicHealth
WELLINGTON-DUFFERIN-GUELPH
Stay Well.

1-800-265-7293
info@wdgpublichealth.ca
wdgpublichealth.ca